


# ለቅቃወ ወገኔ




-በአበራ ለማ



ረሀብ፣ ስቃይ እንግልቱ - መች አንሶህ አንተ ወገኔ

ስደትን ምርኩዝ አድርገህ - መግባትህ ከምድር ኩነኔ?

ምን ሊበጅህ? ምን ሊቤዥህ ? ከቤት እሳት ከደጅ እሳት

ማምለጫ የለህ መሸሸጊያ - መድረሻ የለህ አንዳች ጥጋት፤

ክብር ኩራትህ - እንደራፊ ተላይህ ላይ ተቀዶ

ኢትዮጵያዊ ስምና ሰንደቅ - ማላገጫ ሲሆን እባር ማዶ፤

ማን ያስጥልህ? ማን ይድረስልህ ወገኔ?

ማን ይዋስህ? ማን ይሁንህ ምስለኔ?

ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ

መች ባለ’ዳ ሊል ቢሮሌ?...

የትናንት ትናንት ሕመምህ - ያገርህ ጣውንታት ውጋት

የደርቡሹ፣ የፓሻው፣ ያታቱርኩ ሎሌ የግብጹ ባንዳ ጥቃት-

አያት ቅማያትክን እንዳልበላ - ደሞ ባንተ ላይ ዙሮ መጣ

ያረብ  ዘይቱ ቡላ ብስናት - ስካር አምቡላው ታናቱ ወጣ?

ለካስ የጀማላ ዛር አንጎልም የለው - ቲፈጥረው ኖሮን  አንኮላ

እጎዳና ላይ ሰው አርዶ - ደሙን ጠጥቶ ሥጋውን ቆርጦ ሲበላ፤

ማን ያስጥልህ? ማን ይድረስልህ ወገኔ?

ማና ይዋስህ? ማን ይሁንህ ምስለኔ?

ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ

መች ባለ'ዳ ሊል ቢሮሌ?...

እውን አላህ እግር ጥሎት - ታረብ አገር ሂዶን ኑሯል

እሳኡዲ ጎራ ብሎ - ሳጥናኤልን ጠይቆታል?

"ሰውን ከሰው ለይተህ - ከትፈህ ብላ ብዬሃለሁ?"

እያለ እየጠየቀ -  የራስ ፍጥርቱን እምባ

እሱ ራሱ እያዘራ - እሱ ራሱ እያነባ....

" አላህ አክበር!..." አትበለኝ - ባፍ ጉቦ አትደልለኝ!

መካ መዲናን ጉቦ ሰጥተህ - የድሃ እምባ፣ የድሃ ደም፣ የድሃ ነፍስ አትገብረኝ!

ካንተ ጋር ውልም የለኝ - ንግግር እርቅም የለኝ!... "

እያለ አላህ የማታ ማታ ፍርዱን ሰጥቶ -

ግፉዓን ይቤጁ ይሆን - ስቅየታቸው ግዘፍ ነስቶ?

ያ የጥንት የጠዋቱ ጌታ - ልኡል እግዚአብሄር በርትቶ?

ያለያማ ማን አለው? ማን አለው ደራሽ?

ማን ያስጥለው? ማን ይድረስለት ወገኔ?

ማን ይዋሰው? ማን ይሁነው ምስለኔ?

ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ

መች ባለ'ዳ ሊል ቢሮሌ?...